# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች አስፈላጊነት እና ተግባር

## 1. መግቢያ

የተማከለ የካፒታል ገበያ ስርአት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሪፎርም ወይም ለውጥ አንዱ ማሳያ ነው። የዚህ እየተለወጠ የመጣው የፋይናንስ ስነ-ምህዳር ወሳኝ አካል ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መቋቋም እና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ነው። በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ትርጉም የተሰጠው እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 1031/2017 በኩል ተግባራዊ የተደረገው ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ እና ቁጥጥር አሰራር በገበያ ቁጥጥር ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ተቋም ነው። ይህ ጽሑፍ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶችን አስፈላጊነት፣ ኃላፊነቶች እና የቁጥጥር ማዕቀፍ አጠቃላይ ትንተና ይሰጣል። በቀጥታ ከዋና ዋና የአዋጁ እና የመመሪያው ድንጋጌዎች በመነሳት፣ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የገበያ ታማኝነትን ለማሳደግ፣ ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ የሚጫወቱትን ሚና ይዳስሳል።

## 2. የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ እና የራስ ቁጥጥር አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በአዋጁ መሰረት ከተቋቋሙ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች አንዱ ሲሆን በባለስልጣኑ እውቅና የተሰጠው እና የራሱ አባላት ያሉት ድርጅት ነው። የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ኢንቨስተሮች የረጅም ጊዜ ፋይናንስ ለመሰብሰብ፣ የኢንቨስትመንት እድሎችን ለማስፋት እና የአገሪቱን ግዙፍ የልማት ግቦች ለመደገፍ የተቋቋመ ነው።

*"ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላሎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኞች እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎች ያሉ የግብይት አሳላጮች አባላቱ ላይ የቁጥጥር ስልጣንን የሚጠቀም መንግስታዊ ያልሆነ አካል ነው። "*

የካፒታል ገበያ አዋጅ ለዚህ ገበያ ሕጋዊ መሠረት ፈጥሮ ባለሥልጣኑን እንደ ዋና ተቆጣጣሪ አቋቁሟል። ውጤታማ የቁጥጥር ሥርዓት ባለብዙ ደረጃ አቀራረብን እንደሚፈልግ በመገንዘብ አዋጁ ራስን በራስ የመቆጣጠር ጽንሰ-ሀሳብ አስተዋውቋል።

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት እንደ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላሎች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኞች እና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎች ያሉ የግብይት አሳላጮች አባላቱ ላይ የቁጥጥር ስልጣንን የሚጠቀም መንግስታዊ ያልሆነ አካል ነው። የተወሰኑ የቁጥጥር ተግባራትን ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የማስተላለፍ ምክንያት ብዙ ገፅታ አለው።

ከእነዚህም በተለይ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የኢንዱስትሪ እውቀትን እንዲጠቀም እድሉን ይሰጣል፣ ለተወሰኑ የገበያ ክፍሎች የተበጀ ተለዋዋጭ እና ግልጽ የሆነ ደንብ ማውጣት ያስችላል፣ በባለስልጣኑ ላይ ያለውን ቀጥተኛ የቁጥጥር ጫና ከመቀነስ በዘለለ በኢንዱስትሪው ውስጥ የተገዢነት ባህልን ያበረታታል። መመሪያ ቁጥር 1031/2017 እንደነዚህ ያሉ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚታወቁ፣ እንደሚተዳደሩ እና እንደሚቆጣጠሩ ዝርዝር የእውቅና አሰጣጥ እና የቁጥጥር አሰራር ይዘረጋል። ይህም ባለብዙ

ደረጃ የቁጥጥር ስርዓት የሚዘረጋ ትልቅ እርምጃ መወሰዱን ያሳያል።

## 3. የህግ መሰረት፡ አዋጅ እና መመሪያ

ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የአሠራር ማዕቀፍ ከሁለት ደረጃ ካለው የህግ ማዕቀፍ የተገኘ ነው፡ አንደኛው የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2021 ሲሆን ይህ ዋናው እናት ህግ ነው። የአዋጁ አንቀጽ 22 ባለስልጣኑ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶችን እውቅና የመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን እና የተወሰኑ የቁጥጥር ተግባራትን ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት ውክልና ይሰጣል። በቂ አቅም እና ብቃት፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ የአባልነት ደንቦች እና የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድሙ የአስተዳደር መዋቅሮችን ጨምሮ እውቅና ለማግኘት ዋና ዋና መስፈርቶችን ይዘረዝራል።

ሁለተኛው መመሪያ ቁጥር 1031/2017 ሲሆን ዝርዝር የእውቅና አሰጣጥ እና የቁጥጥር አሰራርን ይደነግጋል። መመሪያው የአዋጁን መርሆዎች የማመልከቻ ሂደቶችን፣ የአስተዳደር ደረጃዎችን፣ ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎችን፣ የቁጥጥር ዘዴዎችን እና የማስፈጸሚያ እርምጃዎችን ዝርዝር ይሸፍናል። ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለመሆን እና ለመስራት ለሚፈልግ ማንኛውም አካል እንደ የህግ ማዕቀፍ እና የቁጥጥር መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

ይህ ማዕቀፍ የውክልና ሥልጣን ግንኙነትን የሚያቋቁም እና ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች እንደ ግንባር ቀደም ተቆጣጣሪዎች ሆነው እንዲሰሩ ነገር ግን ለባለሥልጣኑ ተጠያቂነት ያላቸው እና ቀጣይነት ያለው ቁጥጥር የሚደረግባቸው መሆናቸውን ይገልፃል።

## 4. የእውቅና ሂደቱ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ማቋቋም

መመሪያው ለማንኛውም አካል እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በይፋ እውቅና ለመስጠት ጥብቅ እና ግልጽ የሆነ የእውቅና አሰጣጥ ሂደት ያቋቁማል። ያለባለሥልጣኑ እውቅና እንደ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት መስራት የተከለከለ ሲሆን የእውቅና አሰጣጡም የሚከተሉትን ቁልፍ መስፈርቶች ያካትታሉ፡

**ማመልከቻ አቀራረብ፡** ሰፊ ሰነዶችን የያዘ መደበኛ ማመልከቻ በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ መቅረብ አለበት።

**የሰነድ መስፈርቶች፡** አመልካቹ የምስረታ ሰነዶችን፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ለመከላከል የተዘጋጁ ዝርዝር አሰራር ደንቦች እና ፖሊሲዎች፣ የድርጅታዊ መዋቅር፣ የፋይናንስ እና የአስተዳደር አቅም፣ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እና ለከፍተኛ ባለሙያዎቹ ተገቢ እና ብቁ መሆናቸውን ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት። በተለይም የራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ደንቦች ከዋናው የካፒታል ገበያ አዋጅ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ማሳየት አለበት።

በአመልካቹ እና ከፍተኛ ባለሙያዎቹ የተፈረመ አባላቱ ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ለከፍተኛ ባለሙያዎች እና ከፍተኛ ተጽዕኖ ላላቸው ሰዎች የወጣውን የስነ-ምግባር ደንብ እና ሌሎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ህጎችን ለማክበር የገቡት ስምምነት ማቅረብ፣

**የሰራተኞች ግምገማ፡-** ዋና የህግ ማስከበር መኮንኑን ጨምሮ ቢያንስ ሦስት የአመልካቹ ከፍተኛ ባለሙያዎች ከባለሥልጣኑ ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለባቸው። ይህም ከአመልካቹ ጀርባ ያለው የሰው ኃይል ብቃት ያለው እና ተአማኒ መሆኑን ለመገምገም እና ለማረጋገጥ ይረዳል።

**የእውቅና ውሳኔ ጊዜ፡-** ባለሥልጣኑ ሙሉ ማመልከቻ ከተቀበለ በኋላ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ይህም የእውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት የተቀላጠፈ እንደሚሆን እና በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ የሚያመላክት ነው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

**እውቅና መከልከል፦** መመሪያው እንደ በቂ ያልሆነ አቅም፣ የተሳሳተ መረጃ፣ ደንቦችን አለማክበር፣ የተገቢነት እና ብቁነት መስፈርቶችን አለማሟላትን የመሳሰሉ ውድቅ የማድረጊያ ምክንያቶች ወይም እውቅና የሚያስከለክሉ ምክንያቶች በግልጽ ይዘረዝራል። አንድ አመልካች የእውቅና ጥያቄው ውድቅ ከመደረጉ በፊት የመሰማት መብት ሊሰጠው ይገባል።

ይህ ጥብቅ ሂደት በግልጽ የሚታይ እውቀት፣ ክህሎት እና ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅር ያላቸው እና ተፈትነው ያለፉ ጠንካራ የሆኑ አካላት ብቻ እውቅና እንዲያገኙ የሚረዳ ነው።

## 5. ራስን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅት ሚናዎች፣ ስልጣን እና ተግባራት

አንድ ራስን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅት እውቅና ካገኘ በኋላ ለዕለታዊ የገበያ ቁጥጥር ማዕከላዊ የሆኑ ጉልህ ኃላፊነቶችን ይወስዳል።

**ዋና ግዴታዎች፡** ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ለኢንቨስተሮች ጥበቃ ቅድሚያ መስጠት፣ የገበያ ታዓማኒነትን ማሳደግ፣ የስርዓት አደጋን መቀነስ እና የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳርን ለማዳበር መጣር አለባቸው። ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን ብቻ እንደ አባል እንዲቀበሉ ስልጣን የተሰጣቸው ሲሆን ፍትሃዊ እና ግልጽ የመግቢያ መስፈርቶች እና ሂደቶች ሊኖራቸው ይገባል።

**የውክልና ስልጣን እና ግዴታዎች፡** በባለሥልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የሚከተሉትን የማድረግ ስልጣን አላቸው።

**ደንብ ማውጣት፡** የአባሎቻቸውን ባህሪ እና እንቅስቃሴ መብት እና ግዴታ የሚቆጣጠሩ ደንቦችን ማዘጋጀት እና በባለሥልጣኑ አስጸድቀ ስራ ላይ ያውላል፣

**ቁጥጥር እና ማስፈጸም፡** ለአባላት ዝቅተኛ የአሠራር መስፈርቶችን ያስቀምጣል፣ ከስራ ቦታቸው ላይ በመገኘት ወይም ከስራ ቦታቸው ውጪ ቅኝት እና ምርመራዎችን ያደርጋል፣ የአባላት መዝገቦችን ይገመግማል፣

**ዲሲፕሊን፡** ደንቦቻቸውን በሚጥሱ አባላት ላይ ምርመራዎችን በማካሄድ አባሎቻቸው ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ ጊዜ በመቅጣት ደንቦችን ያስፈጽማል፣

**የገበያ ቁጥጥር፡** የገበያ ክትትል በማከናወን ሊከሰቱ የሚችሉ የግብይት ጥሰቶችን ይመረምራል፣

**የግጭት አፈታት፡** በአባላት ወይም በአባል እና በኢንቨስተር መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ሥነ-ሥርዓት እና ደንቦች ሊኖሩት ይገባል፣

**የደንበኛ ካሳ፡** በባለሥልጣኑ መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት በአባላት ምክንያት ኢንቨስተሮች ላይ የሚደርስን ጉዳት ለመካስ የደንበኛ ካሳ ፈንድ በማቋቋም በገበያው ላይ ያለውን እምነት ያሳድጋል፣

ይህ ሃላፊነት ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት የገበያ ተሳታፊዎችን በመከታተል፣ ተገዢነትን በማረጋገጥ እና ሥርዓት የጠበቁ የግብይት ልምዶችን በማስፈን ረገድ የመጀመሪያው የመከላከያ ስልት አድርጎ ያስቀምጣል።

## 6. የአስተዳደር እና የአሠራር ግዴታዎች

መመሪያው ራስን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅቶች ለአባሎቻቸው ራሳቸውን ችለው እና ለሕዝብ ጥቅም እንዲሰሩ ለማረጋገጥ ጥብቅ የአስተዳደር ደረጃዎችን ያስቀምጣል።

**ገለልተኝነት**: ራስን በራስ የሚቆጣጠር ድርጅቶች በንግድ እንቅስቃሴዎቻቸው እና የቁጥጥር ተግባራት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት መጠበቅ አለባቸው። ይሄውም የንግድ ስራቸውን እና በቁጥጥር ስራቸውን በመለየት የተለያየ የሰው ሃይል መመደብ አለባቸው። ከቁጥጥር ቅጣቶች የሚገኙ መቀጮና የአገልግሎት ክፍያ ለቁጥጥር ዓላማዎች ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። የዚህን አፈጻጸም በተመለከተ ፖሊሲ እና የአሰራር ስርዓት ማውጣት እና መተግበር አለባቸው።

**የአስተዳደር መዋቅር**: ከራሱ ወይም ከአባላቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸውን ቢያንስ አንድ ሶስተኛ

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal

የሚሆኑትን ገለልተኛ ዳይሬክተሮች በቦርድ ውስጥ በማካተት ተጨባጭ ቁጥጥርን ማረጋገጥ አለበት።

**ብቁነት እና ተገቢነት መስፈርቶች**: ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅትም ሆነ ሰራተኞቹ ከፍተኛ የሥነ ምግባር እና የሙያ ደረጃዎችን ማሟላት አለባቸው። ከፍተኛ ባለሙያዎች ከፖሊስ የተሰጠ ከወንጀል ነጻ የምስክር ወረቀት ማቅረብ እና ከዛ በፊት በእነሱ የተፈጸሙ የፋይናንስ ወንጀሎች ሪከርድ፣ ብልሹ አሠራሮች ወይም ኪሳራ ካለ የብቁነት እና ተገቢነት መመዘኛዎች መሰረት ውድቅ ሊደረጉ ይገባል።

**ዋና የህግ ማስከበር መኮንን**: ይህ መኮንን ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት የተገዢ ነት መዋቅር የሥራ ሂደት ዋና ሃላፊ ሲሆን ማንኛቸውንም ጥሰቶች ለባለሥልጣኑ በቀጥታ ሪፖርት ያደርጋል። ይህ የስራ መደብ ከአንድ የስራ ቀን በላይ ክፍት ሊሆን የማይችል ሲሆን ራሱን በራሱ የሚቆጣጠረው ድርጅት የተተኪ ዋና የህግ ማስከበር መኮንን እቅድ ሊኖረው ይገባል፣ ይህም የዚህን የስራ መደብ ሚና ወሳኝ ባህሪ የሚያጎላ ነው።

**ስርዓቶች እና ቁጥጥሮች**: ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር፣ የአደጋ አስተዳደር እና የተገዢነት ስርዓቶችን መተግበር አለባቸው። በቴክኖሎጂ ላይ ለተመሰረቱ በተጠቃሚ ላይ ያተኮረ የግብይት እና ቁጥጥር ሥርዓት ዲዛይን እና የኤሌክትሮኒክ የግብይት ሥርዓቶቹ ላይ መደበኛ የደህንነት ተጋላጭነት ግምገማዎችን ማድረግ አለባቸው።

## 7. በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን የሚደረግ ቁጥጥር ሥርዓት

ራስን በራስ የመቆጣጠር አሰራር ሞዴል የራስ ገዝ ወይም በራስ የመወሰን ሳይሆን የቁጥጥር ውክልና ነው። በዚህ አሰራር ባለሥልጣኑ የመጨረሻውን ስልጣን ይይዛል።

**ቀጣይነት ያለው ቁጥጥር**: ባለሥልጣኑ የራሳቸውን በራሳቸው ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በስራ ቦታቸው ላይ በመገኘት ወይም ከስራ ቦታቸው ውጪ በማሳወቂያም ሆነ ያለማሳወቂያ ቅኝት እና ምርመራ የማካሄድ እና ሁሉንም መዝገቦች የማግኘት ያልተገደበ ስልጣን አለው።

**የሪፖርት ማድረግ ግዴታዎች**: ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በምርመራ፣ በቅኝት፣ በዲሲፕሊን እና በግጭት አፈታት ተግባሮቻቸው ላይ በዝርዝር በየሩብ ዓመቱ እና በየዓመቱ ሪፖርቶችን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም ማንኛውንም የህግ ጥሰቶች ወይም የተጠረጠሩ የገበያ ሸፍጥ ተግባራት ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

**የአስተዳደር እርምጃዎች**: ባለሥልጣኑ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች ብልሹ አሰራር የቅጣት እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚችል በአዋጁ እና በመመሪያው ተመልክቶ ይገኛል። ይህም ቅጣቶችን፣ ማስጠንቀቂያዎችን፣ የግዳጅ የደንብ ማሻሻያዎችን፣ የሰራተኞችን ማንሳትን እና በመጨረሻም እውቅናን ማንሳትን ያካትታል። ይህን ተከትሎ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች በሚወሰድባቸው እርምጃ ቅሬታ ከተሰማቸው ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችሉም ተመልክቶ ይገኛል።

ይህ ማዕቀፍ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የዕለት ተዕለት ቁጥጥርን ሲያደርጉ፣ በግልጽ በተገለጸ የሥልጣን ማዕቀፍ ውስጥ እንደሚሠሩ እና ለአፈፃፀማቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ ያመላክታል።

## 8. ማጠቃለያ

በአዋጁ እና በመመሪያው በኩል ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶችን በሚመለከት የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ማስተዋወቅ ናቸው። በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የቁጥጥር ሥርዓት ከመንግስት-ተኮር ሞዴል ባሻገር የቁጥጥር ስርዓት ሊተገበር እንደሚቻል የሚያመላክት ነው። ይህ ማዕቀፍ የተወሰኑ የፊት መስመር የቁጥጥር ተግባራትን በጥብቅ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ ለባለሙያ እና የኢንዱስትሪው ተሳታፊዎች በውክልና በማስተላለፍ እና የተወሰኑትን ደግሞ በማይለዋወጥ የባለሥልጣኑ ቁጥጥር ስር በማድረግ የግሉ

ዘርፍ ቅልጥፍናን በማጎልበት የኢንቨስተሮችን ጥበቃ፣ የገበያ ፍትሃዊነት እና የፋይናንስ መረጋጋትን በማሳደግ የህዝብ ጥቅም ግቦችን በመጠበቅ ዓላማ ላይ ተመስርቶ በጋራ የገበያውን ደህንነት የማረጋገጥ ሚና መጫዎት የሚያስችል ስለ ምህዳር የሚፈጥር ነው።

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT